ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies(FSS)

የፖሊሲ ፍሬ ኃሳቦች ቁጥር 35

# በመካከለኛው ምስራቅ አገራትና ደቡብ አፍሪካ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የስራ ፈላሲያን ወደ አገር ቤት የሚልኩት ገንዘብና ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አንድምታዎቹ

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ ነክ ምርምሮችን የሚያካሂድ ለትርፍ ያልተቋቋመ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው።

♣ ♣ ♣

የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሠብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል።

♣ ♣ ♣

በድረ-ገጹ የሕትመት ውጤቶቹን ዝርዝር ያቀርባል፤ በልማት ዙሪያ ውይይቶችንም ያካሂዳል።

♣ ♣ ♣

በርዕሱ ዙሪያ ኃሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜል አድራሻችን ላኩልን።

♣ ♣ ♣

ኢሜል፡ fss@ethionet.et

ድረ-ገጽ፡ www.fssethiopia.org

## 1. መግቢያ

ኢትዮጵያን በፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ወደ ልዩልዩ አገራት ይፈልሳሉ። ባለፉት ቅርብ ዓመታት ከኢትዮጵያ ወድ ውጭ የሚደረገው ፍልሰት በከፍተኛ ሁኔታ በመጨመር ላይ ይገኛል። ለሥራ ሲባል የሚደረግ ፍልሠትም በከፍተኛ ሁኔታ በማደግ ላይ ይገኛል። በዚህም ረገድ ከ1980ዎቹ አጋማሽ ዓመታት ጀምሮ በዘይት ኃብት የናጠጡት የአረብ ገልፍ አገራትና በኢኮኖሚ ዕድገት ከአፍሪካ አገራት በላቀ ደረጃ የምትገኘው የደቡብ አፍሪካ ሪፓብሊክ የኢትዮጵያውያን የሥራ ፈላሲያን ዋና መዳረሻ ሆነዋል። ወደ ገልፍ አገራት የሚፈልሱ የሥራ ፈላሲያን ሕጋዊ ዶክመንቶችን የያዙም ያልያዙም ሲገኙበት፣ ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚያመሩት ግን በአመዛኙ ሕጋዊ የጉዞ ሠነዶች ያልያዙ መሆናቸውን ጥናቶች ያመለክታሉ።

በተለያዩ አገራት በቋሚነት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን (ዲያስፖራ) እና በውጭ አገር በሥራ ላይ የተሰማሩ ዜጎች ከሚኖሩባቸው አገራት ቤተሠብን መርዳት ጨምሮ ለኢንቨስትመንት የሚውል ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ወደ አገር ቤት ይልካሉ። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከውጭ አገር የሚላከው የገንዘብ መጠን በከፍተኛ ደረጃ በመጨመሩ ምክንያት ከውጭ የሚመጣው ኃብት (በእንግሊዘኛ አጠራር ሪሚታንስ) ዛሬ ከአገሪቱ ዋና ዋና የውጭ ምንዛሬ ምንጮች መካከል አንዱ ለመሆን ችሏል። ለምሳሌ ውጭ አገር ካሉ ኢትዮጵያውያን ወደ አገር ቤት የተላከው ገንዘብ በ2006 ዓም ከነበረበት 3.04 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በ2008 ዓም ወደ 3.99 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ማደጉን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መረጃ ያመለክታል። ይህ ከፍተኛ ኃብት ወደአገር ውስጥ የሚተላለፍበትን መንገድ በሁለት መክፈል ይቻላል፤ የመጀመሪያው ባንክን በመጠቀም ገንዘብን ማስተላለፍ ሲሆን፤ ይህንን ዘዴ ህጋዊ (ወይም) መደበኛ ማለት ይቻላል። ሁለተኛው መንገድ ባንክን ሳይጠቀሙ በተለያዩ መንገዶች ገንዘብን ወደ አገር ቤት ማስገባት ነው። ይህ መንገድ የመንግሥት የውጭ ምንዛሬ አስተዳድር ደንቦችን ስለሚጥስ መንግሥት ሕገ-ወጥ ብሎ ይፈርጀዋል። ተመራማሪዎችና በዚህ ጉዳይ ላይ የሚሰሩ ዓለምአቀፍ ተቋማት ግን ይህን መንገድ መደበኛ ያልሆነ የማስተላለፊያ ዘዴ በማለት ይጠሩታል።

ከውጭ አገራት ወደ ኢትዮጵያ ከሚገባው ገንዘብ አብዛኛው መደበኛ ባልሆነ መንገድ እንድሚገባ ይታወቃል። አንድ በውጭ አገር ያለ ኢትዮጵያዊ ወደ አገር ቤት ገንዘብ በሚልክበት ጊዜ ከሁለቱ አማራጮች አንዱን ለመጠቀም የሚወስነው በተለያዩ ምክንያቶች ሲሆን፤ ከነዚህ ምክንያቶች መካከል የላኪው ግለሰብ በፍልሰት በሚገኝበት አገር ሕጋዊ ሠነድ ያለው መሆኑ ወይም አለመሆኑ፤ በሁለቱ የገንዘብ ማስተላለፊያ መንገዶች መካከል ያለው የምንዛሬ ልዩነትንና በአገር ውስጥ የባንክ አገልግሎት ተደራሽነት ውስን መሆን ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ከውጭ የሚመጣው ገንዘብ የሚቀበሉ ቤተሰቦች ገንዘቡን በአመዛኙ ለቤት ውስጥ ፍጆታ እንደሚያውሉትም የተለያዩ ጥናቶች ያሳያሉ።

## 2. የጥናቱ ዓላማና ዘዴ

የዚህ ጥናት ሀለት ተዛማጅ ዋና ዋና ዓላማዎች ያሉተ ሲሆን የመጀመሪያው በውጭ አገር በተለይም በገልፍ አገራትና በደቡብ አፍሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወደ አገር ቤት ገንዘብ ለመላክ በመደበኛናና መደበኛ ካልሆኑት የመላኪያ ዘዴዎች መካከል አንዱን ወይም ሌላውን የሚመርጡባቸው ምክንያቶች መረዳትና፤ ሁለተኛ ደግሞ ከውጭ የሚመጣው ገንዘብ ተቀባይ ቤተሰቦች እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚያውሉት መመርመር ናቸው።

በተጨማሪም ጥናቱ ተጨባጭ መረጃዎችን በመተንተን ከውጭ አገር የሚመጣው ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ለአገርና ለቤተሰብ ዕድገት የበለጠ አስተዋኦ እንዲያበረክት ለማስቻል የሚጠቅሙ የፖሊሲ ምክረ-ኃሳቦች ይሰነዝራል።

ለዚህ ጥናት ግብዓት የሆኑ መረጃዎች የሥራ ፈላሲያን ዋና ምንጭ ከሆኑ አምስት ዋና ዋና ክልሎች (ትግራይ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦችና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር) በስልት ከተመረጡ ሁለት ሁለት ወረዳዎች በጠቅላላው አስር ወረዳዎች ተሰብስበዋል።

የተለያዩ የጥናት ቡድኖችን በማዋቀርና የተለያዩ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች በመጠቀም በተመረጡት ወረዳዎች ለሰባት ሳምንታት (ከጥር 7 ቀን 2010 እስከ

ሚያዝያ 23 ቀን 2010) በቆየ የመስክ ሥራ ልዩ ልዩ አኃዛዊና ሀተታዊ መረጃዎን ማሰባሰብ ተችሏል፡፡ የጥናቱ የመረጃ ምንጮች የሚከተሉትን ያካትታል፡፡ በዚህም በውጭ አገራት ከሁለት ዓመታት ሳላነሰ ጊዜ በሥራ ፈላሲነት ቆይተው ከተመለሱ ተመላሾች መካከል ከየወረዳዎቹ 25 (በድምሩ 250) ተመላሾችን በናሙናነት በመምረጥ በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ምላሽ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ከቤተሰብ አባላት መካከል ከየወረዳው 20 (በድምሩ 200 የፈላሲ ሠራተኞች ቤተሰቦች) ከውጭ አገር የሚላክ ገንዘብን በተመለከተ መረጃዎች እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የጥናት ቡድኑ አባላት ቁልፍ መረጃ መስጠት የሚችሉ ግለሰቦችን በሁሉም በጥናቱ በተካተቱት ወረዳዎች/ቦታዎች አነጋግረዋል፡፡ ልዩ ልዩ የታተሙና ያልታተሙ ጥናቶችና ሪፖርቶችም የመረጃ ምንጭ በመሆን አገልግለዋል፡፡

## 3. የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች

### 1.1 ከገልፍ አገራትና ደቡብ አፍሪካ የሚላክ ገንዘብ

በጥናቱ ከተካተቱት ተመላሾች መካከል ከሞላ ጎደል ሁሉም (97%) ውጭ በሥራ ላይ ተሰማርተው ከነበሩበት አገራት ለቤተሰቦቻቸው ገንዘብ ይልኩ ነበር፡፡ በተመሳሳይም ሁኔታ ከፈላሲያን ቤተሰቦች መካከል 92% የሚሆኑት ውጭ አገር በሥራ ተሰማርተው ከሚገኙ የቤተሰብ አባላት ገንዘብ በመደበኛ ሁኔታ እንደሚላክላቸው ገልጸዋል፡፡ ሁሉም ፈላሲያን አቅማቸው በፈቀደ መጠን ወደቤተሰቦቻቸው ገንዘብ የሚልኩበት ዋናው ምክንያት ፈላሲያኑ ከመጀመሪያውኑ ከአገር ሲወጡ የራሳቸውንና የቤተሰቦቻቸውን ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ውጭ አገር ሥራ በመሥራት ለመቀየር በመሆኑ ነው፡፡ ፈላሲያኑ በዋናነት መቼና እንዴት ገንዘብ እንደሚልኩ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ 34.3% የሚሆኑት ተመላሾችና 36.0% የሚሆኑት የፈላሲያን ቤተሰቦች ገንዘብ በመደበኛነት በየጊዜው እንደሚላክ ሲገልጹ፤ 36.3% ተመላሾችና 32.5% ቤተሰቦቻቸው ገንዘብ በሚያስፈልግ ጊዜ እንደሚላክ ገልጸዋል፡፡ ለህክምና፣ ለልጆች ትምሕርት ቤት ክፍያ፣ ለዘርና ለማዳበሪያ መግዣ፣ ለቤት መስሪያና ጥገና እንዳስፈላጊነቱ ገንዘብ ከሚላክባቸው ምክንያቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ እንዲሁም ፈላሲያኑ እንደ እንቁጣጣሽ፣ መስቀል፣ ፋሲካ፣ ኢድ አልፈጥር እና ኢድ አል አድሀ (አረፋ) ለመሳሰሉ በዓላት የሚውል ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ለቤተሰቦቻቸው እንደሚልኩ ለዚህ ጥናት መረጃ ከሰጡ የባንክ ኃላፊዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

### 1.2 የገንዘብ መላኪያ መንገዶች

በመደበኛና መደበኛ ያልሆነ የገንዘብ መላኪያ መንገዶች የየራሳቸው መልካምና ጎጂ ጎኖች አሏቸው፡፡ በጥናቱ ከተካተቱት ተመላሾች መካከል 50% የሚሆኑት በዋናነት እንደ ዌስተር ዩኒየንና መኒ ግራም የመሳሰሉ መደበኛ የመላኪያ መንገዶችን በዋናነት ይጠቀሙ አንደነበር ሲገልጹ፣ የቀሩት 50% መደበኛ ያልሆኑ መንገዶች ይጠቀሙ አንደነበረ አመልክተዋል፡፡ በሌላ በኩል በጥናቱ ከተካተቱት ቤተሰቦች መካከል አብዛኛዎቹ (72%) ከውጭ የሚመጣላቸው ገንዘብ በመደበኛ መንገድ (በባንኮች) እንደሚደርሳቸው ሲገልጹ፤ የተወሰኑት (28%) መደበኛ ባልሆኑ መንገዶች እንደሚላክላቸው አስረድተዋል፡፡ የፈላሲያን ቤተሰቦች አብዛኛውን ጊዜ ከውጭ የሚመጣ ገንዘብ በባንክ እንደሚደርሳቸው መግለጻቸው የመደበኛው የገንዘብ መላኪያ ዘዴን ዕድገት የሚያመክት ሳይሆን፣ በተቃራኒው ህገ-ወጥ የገንዘብ አስተላላፊዎች በአገር ውስጥ እየተስፋፉ የመጣውን የባንክ አገልግሎት በመጠቀም ሥራቸውን አንዴት አንደሚያቀላጥፉ የሚያሳይ ማስረጃ ነው፡፡

#### መደበኛ የገንዘብ ማስተላለፊያ መንገዶች

ከፍልሠት ተመላሾች እንደሚገልጹት መደበኛው የገንዘብ መላኪያ መንገድ እጅግ አስተማማኝ ከመሆኑም በተጨማሪ በመደበኛ መንገድ የሚላከው ገንዘብ በባንኮች በኩል የሚመጣ በመሆኑ ለአገሪቱ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት ለብሔራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት የራሱን ድርሻ ያበረክታል፡፡ ምንም እንኳን አስተማማኝነቱና ለአገር ዕድነት ያለው አስተዋጽኦ የላቀ ቢሆንም መደበኛውን የገንዘብ ማስተላለፊ በሚገባ ለመጠቀም የማያስችሉ ተግዳሮቶችም ይታዩበታል፡፡

የመጀመሪያው ተግዳሮት በተለያዩ አገራት የሚገኙ ፈላሲያን ገንዘብ በባንኮች በኩል ለመላክ ፓስፖርት፣ የመኖሪያና የሥራ ፈቃድና የመሳሰሉ ሕጋዊ ሠነዶችን ማቅረብ መገደዳቸው ነው፡፡ ብዛት ያላቸው በመካከለኛው ምስራቅና ደቡብ አፍሪካ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሕጋዊ ሠነድ ያልያዙ በመሆናቸው ባንኮችን በመጠቀምገንዘብ መላክ ይሳናቸዋል፡፡ በጥናቱ ከተጠየቁት ተመላሾች መካከል 40.4% የሚሆኑት ውጭ አገር በነበሩበት ጊዜ ህጋዊ የመኖሪያ ፈቃድ ስላልነበራቸው ባንክ ገንዘብ ለመጠቀም ዕንቅፋት እንደሆነባቸው አመልክተዋል፡፡

መደበኛ ማስተላለፊያ መንገዶችን መጠቀምን የሚያዳክመው ሁለተኛው ተግዳሮት ደግሞ በመደበኛና መደበኛ ባልሆነው (በጥቁር ገበያ) መካከል ያለው የምንዛሬ ልዩነት ነው፡፡ በዚህ ረገድ በጥናቱ ከተካቱት ተመላሾች መካከል 26.8% የሚሆኑት የምንዛሬ ልዩነቱ በባንክ ገንዘብ ለመላክ እንደማያበረታታ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም የመደበኛ የገንዘብ ማስተላለፊያ ተቋማት አሠራር ውስብስብነት (14.0 %) በአራተኛነት የተጠቀሰ ተግዳሮት ሲሆን አብዛኛዎቹ ወደተጠቀሱት አገራት የሚጓዙ ፈላሲያን የትምህርት ደረጃ አነስተኛ መሆኑና የፈለሱባቸውን አገራት ቋንቋ የመናገር ችሎታቸው ውስን መሆኑ ግምት ውስጥ ሲገባ ተግዳሮቱ ከፍተኛ ዕንቅፋት እንደሚሆን ይገመታል፡፡ ባንኮች ገንዘብ ለማስተላለፍ የሚያስከፍሉት የአገልግሎት ዋጋ ከፍተኛ መሆን (5%) እና የባንክ አገልግሎት በተቀባይ ቤተሰቦች አካባቢ ያለው ተደራሽነት ውስን መሆን (7.0%) ሌሎች በመካከለኛው ምስራቅ አገራትና ደቡብን አፍሪካ ያሉ ኢትዮጵያውያን መደበኛ የገንዘብ ማስተላለፊያ መንገድን በመጠቀም ገንዘብ እንዳይልኩ ከሚያግዱ ምክንያቶች መካከል መሆናቸው ተጠቁሟል፡፡

#### መደበኛ ያልሆኑየገንዘብ ማስተላለፊያ መንገዶች

መደበኛ ያልሆኑ የገንዘብ መላኪያ መንገዶች የሥራ ፈላሲያኑ ለቤተሰቦቻቸው ገንዘብ ለመላክ በስፋት የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች ናቸው፡፡ ከመደበኛ የገንዘብ ማስተላለፊያ ዘዴ በተቃራኒ መደበኛ ያልሆኑ የገንዘብ ማስተላለያ ዘዴዎች ከላኪና ተቀባይ አገራት የባንክ አሠራርና የገንዘብ ፖሊሲ ውጪ ላኪ፣ ተቀባይና አስተላላፊዎች በየፊናቸው በሚያገኟቸው የጥቅም ትስስር ሳቢያ የሚካሄድ ተግባር ነው፡፡ ቅልጥፍና፣ አነስተኛ የማስተላለፊያ ዋጋና ተደራሽነት የአሰራሩ ዋና ዋና መገለጫዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም በመካከለኛው ምስራቅ አገራትና ደቡብ አፍሪካ ያሉ ኢትዮጵያውያን በተለያዩ መደበኛ ባልሆኑ የገንዘብ መላኪያ መንገዶች በስፋት ሲጠቀሙ ይስተዋላል፡፡ በዚህ ጥናት ከተካተቱት ተመላሾች መካከል 50% እንዲሁም በጥናቱ ከተካተቱት ቤተሰቦች መካከል 28% የሚሆኑት በዋናነት መደበኛ ያልሆኑ የገንዘብ መላኪያ መንገዶች እንደሚጠቀሙ ገልጸዋል፡፡ መደበኛ ካልሆኑት የገንዘብ ማስተላለፊያ መንገዶች መካከል በተለምዶ ‹‹ሀዋላ›› በመባል የሚታወቀው ዋነኛው ሲሆን በዚህ ዘዴ ገንዘቡ በሚላክበት አገር የሚገኝ ‹‹አስተላላፊ›› ከላኪው ገንዘቡን በውጭ ምንዛሬ በመቀበል አገር ውስጥ ባለ ወኪሉ አማካይነት ለተቀባዩ በብር የሚሰጥበት አሠራር ነው፡፡ ፈላሲያን ይህንን መደበኛ ያልሆነ የመላኪያ መንገድ በሶስት ዋና ዋና ምክንያቶች እንደሚመርጡት ታውቋል፡፡ የመጀመሪያው በዚህ ዘዴ የሚላክ የውጭ አገር ገንዘብ በመደበኛ መንገድ ከሚላከው የተሻለ ምንዛሬ ማስገኘቱ ሲሆን፤ በሁለተኛነት ‹‹ሀዋላ›› መላኪያ ዘዴ ፈጣንና ቀልጣፋ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ በዚህ ዘዴ የሚላክ ገንዘብ በአማካይ ከሁለት ቀን

ባልበለጠ ጊዜ ተቀባዮች ዘንድ እንደሚደርስ ይነገራል፡፡ መንገዱ ቀላል፣ ቀልጣፋና ምንም ዶክመንት የማያስፈልገው መሆኑ ዘዴውን የሚያስመርጠው ሶስተኛው ምክንያት ነው፡፡ በተጨማሪም የባንኮች እና ሞባይል ቴሌፎን አገልግሎት በአገሪቷ መስፋፋት ለ‹‹ሀዋላ›› መላኪያ ዘዴ መስፋፋትና መጠናከር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጉን መረዳት ይቻላል፡

### 1.3 ከውጭ የሚመጣ ገንዘብ በቤተሠብ ደረጃ ያለው አበርክቶት

ከውጭ የሚመጣን ገንዘብ ተቀባዮች እንደገንዘቡ መጠንና እንደኑሯቸው ሁኔታ ለተለያዩ አግልግሎቶች ይጠቀሙበታል፡፡ ከእነዚህ ግልጋሎቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ሆነው ተገኝተዋል፡-

#### ብድር መክፈልና ንብረትን መልሶ ማደራጀት

በአብዛኛው ጊዜ ደሀ ቤተሰቦች ከውጭ አገር የሚላክላቸውን ገንዘብ ከሌሎች ነገሮች ቅድሚያ በመስጠት የፈላሲያኑን የጉዞ ወጪ ለመሸፈን ቤተሰብ የገባውን ብድር ለመክፈል ወይም በመያዣነት የተያዘ ንብረት ለማስመለስ ይጠቀሙበታል፡፡ በጥናቱ ከተካተቱት ተመላሾች መካከል 20% ለጉዟቸው የሚያስፈልጋቸውን ገንዘብ በብድር ያገኙ መሆናቸውን ገልጸው፤ ከውጭ የላኩት ገንዘብ በቅድሚያ ብድር ለመክፈል መዋሉን አስረድተዋል፡፡

#### የቤተሠብ የዕለት ተዕለት ፍጆታ

ዕዳ ከመክፈል በመቀጠል ከውጭ የሚመጣ ገንዘብ የቤተሰብን የዕለት ተዕለት ፍጆታን ለሟሟላት ይውላል፡፡ ይህ የፍጆታ ወጪ የቀለብና ሌሎች ወጪዎችን እንዲሁም ከጤና እና ትምህርት ወጪዎች አንስቶ እስከ የቤት ቁሳቁስ ግዢ ያካትታል፡፡ በጥናቱ ከተካተቱት የፈላሲያን ቤተሰቦች መካከል 53.5% የሚላክላቸውን ገንዘብ በዋናነት ምግብን ጨምሮ የቤት ውስጥ ፍጆታዎችን ለሟሟላት፣ የልጆች ትምህርት ወጪን ለመሸፈን፣ ለልብስና ለህክምና እንደሚያውሉት ገልጸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተለይ በከተሞች አካባቢ ውጭ በሥራ ላይ የተሰማሩ የቤተሰብ አባላት በሚልኩት ገንዘብ ቴሌቪዥን፣ ዲሽና ማቀዝቀዣ የመሳሰሉ የቤት ዕቃዎች እንደሚገዙበት ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ከውጭ በሚመጣው ገንዘብ የመኖሪያ ቤትን ማደስ በተለይ በአዲስ አበባና ሌሎች ከተሞች የተለመደ ተግባር ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከውጭ የሚላክ ገንዘብን አለመቆጠብና ቀጣይነት ባለው የኢንቨስትመንትሥራ ላይ አለማዋል ተቀባይ ቤተሰቦችን ለዘወትር ተረጂነት ይዳርጋል፡፡ በዚህ ሳቢያ ለረጅም ጊዜ በሰው አገር ሲለፉ ቆይተው ወደአገራቸው ሲመለሱ ሲልኩ የቆዩት ገንዘብ ባክኖ ለችግር የሚዳረጉ ተመላሾች ቁጥር ቀላል እንዳልሆነ መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ፡፡ በዚህ ሳቢያ አያሌ ተመላሾች መንግሥት ወጣቶችን በማህበራት በማደራጀት ሥራ እንዲጀምሩ ለማስቻል የሚሠጠውን የብድርና ሌሎች ድጋፎችን ለማግኘት በእነርሱ በኩል ማሳየት ያለባቸውን ውስን ገንዘብ ለማግኘት እንደሚቸገሩ በዘርፉ የሚሰሩ ባለሙያዎች ያስረዳሉ፡፡

#### ንብረት ማፍራትና አዲስ ሥራ መጀመር

አብዛኛዎቹ ተጠያቂዎች ከውጭ የሚላክላቸውን ገንዘብ ለፍጆታ ቢያውሉትም፤ የተወሠኑት ቤተሰቦች ግን የሚመጣላቸውን ገንዘብ ለቁጠባና ንብረት ለማፍራት ማዋላቸውን መረዳት ተችሏል፡፡ ከተጠያቂ ቤተሠቦች መካከል በጣም ጥቂቶቹ (3.5%) ከውጭ በሚመጣላቸው ገንዘብ ቁጠባ ማድረጋቸውን ሲገልጹ፤ የቀሩት ገንዘቡን የኮንዶሚኒየም ቤት ቁጠባ ክፍያ (1.5%)፣ አነስተኛ ንግድ ሥራ ለመጀመር (1.4%)፣ መጠነኛ ሱቅ ለመክፈት (1.4%)፣ የእርሻ በሬና የግብርና ግብዓት ለመግዛት እና ቤት ለመሥራት በመሳሰሉ ላይ እንደሚያውሉት ገልጸዋል፡፡

ጥናቱ ከውጭ የሚላክ ገንዘብን ንብረት ማፍራት ላይ ማዋል በቤተሠቡ ላይ አዎንታዊ ለውጥ እንደሚያስከትልም አመልክቷል፡፡ ለምሳሌ መሬት እያላቸው በእርሻ በሬ ዕጦት ምክንያት የእኩል አርሻ ሥራ ውስጥ ለመግባት ይገደዱ የነበሩ ቤተሰቦች ከውጭ በሚመጣላቸው ገንዘብ በሬ በመግዛት ራሳቸውን መቻላቸውን በመስክ መረጃ ስብሰባ ወቅት ማወቅ ተችሏል፡፡

ከውጭ በሚመጣ ገንዘብ ቤተሰቦች ከሚያፈሯቸውን ንብረቶች አይነት ስንመለከት በከተማና በገጠር አካባቢዎች መካከል ልዩነቶች ይስተዋላሉ፡፡ በትላልቅ ከተሞች እንደባጃጅና አነስተኛ ታክሲ የመሳሰሉ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎችን መግዛት በስፋት ሲታይ፤ በገጠር አካባቢ ቤት መስራት ዋና የንብረት ማፍሪያ መንገድ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡ ቤት መስራት በመካከለኛ ከተሞችና በገጠር በስፋት የሚታይ ቢሆንም ንብረቱን ለብክነት የሚዳርጉ አንዳንድ ተግዳሮቶች ይታያሉ፡፡ በነዚህ አካባቢዎች ከውጭ በሚመጣ ገንዘብ ከሚመለከታቸው የመንግሥት መ/ቤቶች ሕጋዊ ፈቃድ ሳያገኙ ብዙ ቤተሰቦች በህገ-ወጥ መንገድ በተያዙና በተገዙ ቦታዎች ላይ ቤት መስራት የተለመደ ተግባር ነው፡፡ ይህም ቤቶቹ በሕገ-ወጥነት ተፈርጀው የመፍረስና ገንዘቡና ንብረቱም የመባከን አደጋ እንዳለበት ብዙ ቤተሰቦችና ተመላሾች አስረድተዋል፡፡ በሁለተኛነት ከውጭ በሚላክ ገንዘብ በሚፈራው ቤትና ንብረት ባለቤትነት ምክንያት ፈላሲያኑን ጨምሮ በቤተሰብ አባላት መካከል የሚነሳው አለመግባባት በስፋት ይጠቀሳል፡፡ ፈላሲያኑ በውጭ አገር በመሆናቸው ቤቱና ንብረቱ የሚገዛውና የሚሰራው በሌላ የቤተሰብ አባል ስም በመሆኑ ፈላሲያኑ ከውጭ በሚመለሱበት ወቅት ንብረቱን የቤተሰብ አባላት በሚፈጽሙት ክዳት ምክንያት መረከብ ሲያቅታቸው ማየት የተለመደ ሆኗል፡፡ በዚህም በውጭ አገር ሆነው ገንዘብ ልከው የገዙትና ያሰሩት ንብረት ላይ ሕጋዊ የባለቤትነት ሠነድ ስለሌላቸው ንብረቱን በህግ ማግኘት አቅቷቸው ባዶ እጃቸውን የቀሩ የሥራ ፈላሲያን በየአካባቢው ማግኘት አይከብድም፡፡

## 3 የፖሊሲ ምክረ-ኃሳቦች

ጥናቱ ከላይ የተዘረዘሩትን ችግሮች በመተንተን ከውጭ አገራት በኢትዮጵያውያን የሚላከው ገንዘብ በመደበኛ የመላኪያ መንገዶች እንዲመጣ፤ እንዲሁም ይህ ከፍተኛ ኃብት ለቤተሰብ የተሻለ ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ ጠቀሜታ እንዲያስገኝ ለዋና ዋና ባለድርሻ አካላትን የሚከተሉትን ቁልፍ ምክረ-ኃሳቦች ይሰነዝራል፡፡

### ሀ. ለኢትዮጵያ መንግሥት፡-

- የኢትዮጵያ መንግሥት ፍልሰትን የተመለከቱ ሥራዎችን በተቀናጀ መንገድ ለመምራት የሚያስችል ፖሊሲ መቀየሥ ይገባዋል፡፡ የሚወጣው ፖሊሲ በዓለም አቀፍ የሥራ ገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ የሆነ የሰው ኃይል ማፍራት ሒደት ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡ መንግሥት ዜጎች ተመጣጣኝ ክፍያ፣ ጤናማ የሥራ ሁኔታና ህጋዊ ጥበቃ የሚያገኙበት ደህንነቱ የተጠበቀ ሕጋዊ የሥራ ፍልሰትን ማበረታት ይኖርበታል፡፡ ይህንን ማድረግ ህጋዊ ሒደቶችን ሳያሟሉ ለመጓዝ የሚወስኑ ዜጎችን ብዛት ለመቀነስ ከመርዳቱም በላይ፤ በህጋዊ መንገድ የተጓዙት ፈላሲያን ለገንዘብ አስተላላፊ ተቋማት ያላቸውን ተደራሽነት በማስፋት በመደበኛ የገንዘብ ማስተላለፊያ መንገድ የሚመጣውን ገንዘብ መጠን ለመጨመር ይረዳል፡፡
- የኢትዮጵያ መንግሥት ዜጎች የሥራ ፈላሲያንን በብዛት ከሚቀበሉ የመካከለኛው ምሥራቅ እና ሌሎች መዳረሻ አገራት ጋር የሁለትዮሽ የሥራ ስምምነት ውል (Bilateral Labour Agreements) ማድረግና ውሎቹን ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ እነዚህ ስምምነቶች ህጋዊና ደህንነቱ የተጠበቀ የሥራ ፍልሰትን ለማበረታታት ዓይነተኛ መሳሪያ ከመሆናቸው ባሻገር

በውጭ አገራት በሥራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ዜጎችን ደህንነት ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡

- መንግስት ለሥራ ወደውጭ አገራት የሚሄዱ ዜጎች የፋይናንስ ዕውቀትን ለማጎልበት የሚረዳ ሥልጠና የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡ ሥልጠናው ፈላሲያኑ ለሥራ በሚሄዱበት አገር ስለሚኖራቸው የገንዘብ አያያዝ ከወዲሁ እንዲያስቡበት ከማድረጉ በላይ በሚሄዱበት አገር የባንክ ሒሳብ ስለመክፈት፣ ስለቁጠባና አማራጭ የገንዘብ ማስተላለፊያ ዘዴዎች ተገቢው ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያስችላል፡፡
- የፌዴራልና የክልል መንግሥታት እንዲሁም በተዋረድ ያሉ የመስተዳድር አካላት በተለያዩ አገራት ለፍተው ገንዘብ ከሚልኩ ዜጎች በህጋዊ መንገድ ገንዘብ የሚቀበሉ ቤተሰቦቻቸው በህጋዊ መንገድ የመኖሪያ ቤቶች መሥራት የሚችሉባቸውን መንገዶች ማመቻቸት ይኖርባቸዋል፡፡ ለዚህም የሥራ ፈላሲያንና ቤተሰቦቻቸው የቤቶች ሥራ ማኅበራትን እንዲቋቋሙ በመርዳት ቤቶችን በመገንባት ከውጭ አገራት የሚመጣው ገንዘብ ንብረት ማፍራት ላይ እንዲውል ማበረታታት ይቻላል፡፡
- የፌዴራልና የክልል መንግሥታትና በተዋረድ ያሉ የመስተዳድር አካላት የክህሎት ሥልጠናና የብድር አገልግሎቶችን በመስጠት ከውጭ አገራት የሚመጣው ገንዘብ ከፍጆታ ባሻገር ተጨማሪ ገቢ በሚያስገኙ ሥራዎች ላይ እንዲያውሉት ማበረታታት ይኖርባቸዋል፡፡
- መንግሥት በመደበኛውና መደበኛ ባልሆነው የውጭ ገንዘብ ምንዛሬ መካከል ያለውን ክፍተት ለማጥበብ የሚያስችል በሚገባ የታሰበበት የፖሊሲ አቅጣጫና የአሰራር ሒደት ሊቀይስ ይገባል፡፡

**ለ. ለሥራ ፈላሲያን ተቀባይ አገራት፡-**

- ህጋዊና ደህንቱ የተጠበቀ የሥራ ፍልሰት እንዲሰፍን ማበረታታት፤
- ተቀባይ አገራት የሥራ ፈላሲያን መብቶች ለመጠበቅ ይረዳ ዘንድ የወጡትን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በህጋቸው ውስጥ በማካተት የሥራ ፈላሲያን መብትና ደህንነት እንዲጠበቅ ማድረግ፤
- ተቀባይ አገራት ህጋዊ ሒደቶችን ሳያሟሉ በአገሮቻቸው በሥራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ዜጎች ሒደቶቹን አሟልተው ህጋዊ የሚሆኑበትን መንገድ ማመቻቸት፡፡ ይህን ማድረግ የሥራ ፈላሲያንን ለችግር ተጋላጭነት ከመቀነሱ በላይ ህገ-ወጥ የሥራ ስምሪትን ለመቀነስ ይረዳል፡፡
- ተቀባይ አገራት የሥራ ፈላሲያን ገንዘባቸውን በመደበኛ የገንዘብ ማስተላለፊያ መንገድ የሚልኩበትን መንገድ ማመቻቸት፡፡ ለዚህም ከኢትዮጵያ መንግሥት ቆንስላዎች ጋር በመቀናጀት የሥራ ፈላሲያኑ በመደበኛ የገንዘብ አስተላላፊ ተቋማት ዘንድ ተቀባይነት ያለው የመታወቂያ ካርድ እንዲያገኙ ማድረግ አንዱ አማራጭ ይሆናል፡፡

**ሐ. ለገንዘብ ተቋማት፡-**

- የኢትዮጵያ ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ተቋማት የሥራ ፈላሲያን ለመደበኛ የገንዘብ አስተላላፊ ተቋማት ያላቸውን ተደራሽነት ለማስፋት በትብብር መስራት፤
- የኢትዮጵያ ባንኮችና የገንዘብ ተቋማት ከሌሎች የገንዘብ አስተላላፊ ተቋማት ጋር በጋራና በትብብር በመስራት ከውጭ የሚመጣን ገንዘብ ለማስተላለፍ የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ ተመጣጣኝ የሚሆንበትን መንገድ መሻት፤
- አሁን ካሉት የተለያዩ ማትጊያዎች በተጨማሪ በውጭ አገራት ያሉ ኢትዮጵያውያን የሥራ ፈላሲያን ገንዘባቸውን በመደበኛ የመላኪያ ዘዴዎች እንዲልኩ የሚያበረታቱ የገንዘብ አገልግሎቶችና የተሻሉ ማትጊያዎችን በመስጠት ማበረታታት፡፡ በቅርቡ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተለያዩ አገራት ለሚገኙ የዲያስፖራ አባላት በባንኩ ሒሳብ ከፍተው ቁጠባቸውን በውጭ አገር ገንዘብ ሲያስቀምጡ የተሻለ ወለድ የሚያስገኝ አገልግሎት መጀመሩ ይታወቃል፡፡ ይህን የመሰለ አገልግሎት በአረብ አገራትና በደቡብ አፍሪካ በሥራ ላይ ተሰማርተው ለሚገኙ ፈላሲያን ማዘጋጀት ፈላሲያኑ በመደበኛ የገንዘብ መላኪያ መንገድ እንዲጠቀሙ ያበረታታል፡፡

**መ. አለም አቀፍ ድርጅቶችና የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች፡-**

- ህጋዊና ደህናቱ የተጠበቀ የሥራ ፍልሰትን ማበረታታት፤ እንዲሁም መደበኛ ያልሆኑ የሥራ ፈላሲያን መደበኛ የሚሆኑበትን ሒደትና መንገድ ማጥናትና ለሚመለከታቸው አካላት ማቅረብ፣
- የሥራ ፈላሲያን መብትና ደህንነት በምንጭም ሆነ ተቀባይ አገራት እንዲከበር መጎትጎት፤
- የሥራ ፈላሲያን ወደ መዳረሻቸው ከመጓዛቸው በፊትም ሆነ ሲመለሱ ስለ ገንዘብ አያያዝ፣ አጠቃቀምና አላላክ የግንዛቤ ሥልጠና መስጠት፤
- የሥራ ፈላሲያንም ሆኑ ገንዘብ ተቀባይ ቤተሰቦች ከውጭ በሚመጣ ገንዘብ ንብረት ለማፍራት የሚያደርጓቸውን ጥረቶች መርዳት፡፡

አስናቀ ከፋለ እና ዘሪሁን መሐመድ


ምንጭ፡- Asnake Kefale and Zerihun Mohammed ""*Migration, Remittances and Household Socio-Economic Wellbeing: The Case of Ethiopian Labour Migrants to the Republic of South Africa and the Middle East"* FSS Research Monograph No. XX. 2018.



**ምስጋናና ማሳሰቢያ**

ይህ ሠነድ የታተመው በአለም የፍልሰት ድርጅት (IOM) *Caribbean and Pacific- European Union (ACP-EU) Migration Action* በኩል በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ነው፡፡ ለሠነዱ ይዘት ይዘት ሙሉ ኃላፊነቱ የተመራማሪዎቹ ሲሆን በምንም ሁኔታ የአለምአቀፍ የፍልሰት ድርጅትን ወይም የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስን አቋም እንደሚያንጸባርቅ ተደርጎ መወሰድ የለበትም፡፡



§§ አድራሻ፡- ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (FSS) §§ ፖ.ሣ.ቁ.፡- 25864 ኮድ 1000 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

§§ ስልክ፡- 0116 29 78 88/91 §§ ፋክስ፡- 0116 29 78 89 §§ ኢሜል፡- fss@ethionet.et §§ ድረ-ገጽ፡- www.fssethiopia.org